የኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት

በማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት

# የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት

# የአሥራ ሦስት ዓመታት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት

አዲስ አበባ

ግንቦት 1979

## ማውጫ ገጽ


1. የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት አመሠራረት........ 1
2. የጽሕፈት ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት............... 2
3. የጽሕፈት ቤቱ የሥራ አንቅስቃሴ በቅድመ አብዮት..... 3
4. በአብዮቱ ዓመታት የጽ/ቤቱ ድርጅታዊ አቋምና የአሠራር አንቅስቃሴዎች.......................... 4
5. ከ1953 — 1979 በጽ/ቤቱ የተካሄዱ ጥናቶች..... 7
6. የጽ/ቤቱ የኮምፒውተር፣ የማተሚያና የትራንስፖርት አገልግሎት አድገት.................... 25
7. የበጀትና የሰው ኃይል አጠቃቀም ሁኔታ........... 28
8. ያጋጠሙ አበይት ችግሮች...................... 30
9. በኢሕዲሪ ምሥረታ ዋዜማ የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሚገኝበት ሁኔታ.................... 31


Office of the National Committee for Central Planning Central Statistical Office

1. የአስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት አመሠራረት፣

በቅድመ አብዮት የመጀመሪያውን የአምስት ዓመት ፕላን ለማዘጋጀት አስታቲስቲካዊ መረጃዎች አስፈላጊ በመሆናቸውና እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከመስከረም 28 ቀን እስከ ጥቅምት 8 ቀን 1959 በአዲስ አበባ ከተማ የተደረገው የመጀመሪያው የአፍሪካ አስታቲስቲሽያኖች ጉባዔ እያንዳንዱ አገር የራሱን የአምስት ዓመት ፕሮግራም አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ በወሰነው መሠረት በሀገራችን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን የሚያቀርብና የአስታቲስቲክስን ሥራ የሚያስፈጽም ድርጅት በማስፈለጉ ቀድሞ የንግድ፣የኢንዱስትሪና የፕላን ሚኒስቴር ተብሎ ይጠራ በነበረው መ/ቤት ውስጥ እንደ አንድ ክፍል ሆኖ በ1953 የአስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት ተቋቋመ::

በ1955 የራሱ በጀት ተፈቅደለት ሥራውን የቀጠለ ቢሆንም ለአሠራር አመቺ ይሆናል በማለት በ1956 ራሱን የቻለ ድርጅት ሆኖ ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴር ተዛወረ:: እንደገና በ1958 የሥራ ግንኙነት ወደአለው ወደ ፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሲዛወር ይህ ሚኒስቴር ከ1961 ጀምሮ በጠቅላይ ሚኒስቴር የፕላን ኮሚሽን በመባሉ የአስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤትም ኃላፊነቱ ለፕላን ኮሚሽን ሆኖ እስከ 1971 ቆይቷል::

በ1971 ብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ሲቋቋም ጽ/ቤቱ ለዚሁ ተጠሪ ሆኖ ሥራውን በማካሄድ ላይ ይገኛል::

ጽ/ቤቱ ሲመሠረት ከአሥር የማይበልጡ ሠራተኞች እንደነበሩትና በመጀመሪያው ዓመት በጀቱም ከብር 200,000 እንደማይበልጥ የጽ/ቤቱ የታሪክ መዝገብ ያስረዳል::

ጽ/ቤቱ በጊዜው የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር እንዲወጣ በአንድ ዋና ዲሬክተር እንዲመራና አምስት ዋና ክፍሎች እንዲኖሩት ተደርጎ የተዋቀረ ነበር::

እነዚህም:-

- የኢኮኖሚና የሶሻል ክፍል
- የሴንሰስና ሰርቬይ ክፍል
- የጽሑፍ ማዘጋጃ ክፍል
- የአስታቲስቲክስ መረጃዎች ማደራጃ ክፍል
- የአስተዳደር ክፍል ነበሩ::

2. <u>የጽሕፈት ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት፣</u>

የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት ትእዛዝ ቁጥር 79/1964 የእስታቲስቲክስ መረጃዎች ለዕቅድና ፕሮግራም ዝግጅት ለፖሊሲ ቀያሽ አስፈላጊ መሆናቸውንና የእስታቲስቲክስንም ሥራ የሚያስፈጽም ብሔራዊ ድርጅት ማቋቋም አስፈላጊ እንደሆነ ይጠቅሳል፡፡

በተለይም የጽ/ቤቱን ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የሚከተሉት ነጥቦች ተጠቅሰዋል፡፡

1ኛ/ በእስታቲስቲክስ ጉዳይ ሁሉ በጠቅላላው ለመንግሥት ምክር መስጠት፣

2ኛ/ የእስታቲስቲክስ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተን፣ በጽሑፍ ማውጣትና ማሠራጨት፣

3ኛ/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ቀጠራ፣ የእስታቲስቲክስ ጥናትና ምርምር ማዘጋጀትና መምራት፣

4ኛ/ የእስታቲስቲክስ ትርጉምና መደብ ማውጣትና መፈጸሙንም ማረጋገጥ፣

5ኛ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የእስታቲስቲክስ አሠራር ሥርዓት መወሰን፣ የሚሰበሰበውን መረጃ ዓይነትና ዝርዝር፣ የሚሰበሰብበትን ጊዜና ፎርም መመርመርና መፍቀድ፡፡

እነዚህ የተጠቀሱት ተግባርና ኃላፊነት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ሌሎችም ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚያመለክቱና በአዋጅ ቁጥር 303/64 የጽ/ቤቱ ሥልጣን ተገልጿል፡፡

.../3

3. <u>የጽሕፈት ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ በቀድሞ አብዮት፣</u>

የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት በቀድሞ አብዮት ለአሥራ አራት ዓመታት ያህል የሥራ እንቅስቃሴ ሲያደርግ የቆየ ቢሆንም ጽ/ቤቱ ከተመሠረተበት ዓላማ፣ ከሚጠበቅበት ኃላፊነትና ተግባር አኳያ ሲታይ የፊውደ ቡርዠው ሥርዓት ለአስታቲስቲክስ ሥራ ለይስሙላ አቅድ ከማውጣት ሌላ በበጀት፣ በሰው ኃይልና በአሠራር አምብዛም ትኩረት ያልሰጠው በመሆኑ የጽ/ቤቱ እንቅስቃሴ ውሱን እንዲሆን አድርጓታል፡፡ ይሰበሰብ የነበረው አስታቲስቲካዊ መረጃም ያልተሟላና በተወሰኑ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዘርፎች ላይ ብቻ ያተኮረና ጥናቶችም ያለ ዕቅድ በግብታዊነት ይካሄዱ እንደ ነበር መታወቅ ይኖርበታል፡፡

የተከናወኑት ተግባሮችም ከጽ/ቤቱ ከሚጠበቀው ኃላፊነትና ተግባር ጋር ሲነጻጸር ኋላ ቀርና እድገት ያልታየበት መሆኑ ብያጠያይቅም፣ ለዚህ ኋላቀርነት ዋና ምክንያት የጽ/ቤቱ ድርጅታዊ ጥንካሬ ለብዙ ዓመታት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት ብቻ ባይሆን በቀድሞ አብዮት ኢትዮጵያ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ አውታር የሆኑትን የልማት ዘርፎች በፕላን የመምራቱና የመቆጣጠሩ ባሕል ባለመዳበሩ የተነሳ፣ ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ያለው አስታቲስቲክስም አስፈላጊነቱና ጠቃሚነቱ በሚገባ መልኩባለመታወቁ ጭምር በእድገቱ ላይ ተጽእኖ ሊኖረው ችሏል፡፡

በዚህ ኋላ ቀር የእድገት ሁኔታ ለተወሰኑ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዘርፎች ሲሰበሰብ የቆየው አስታቲስቲካዊ መረጃ ቀጥራቸው የተወሰኑትን ሠራተኞች አዲስ አበባ ብቻ ከሚገኘው ጽ/ቤት ወደ አስፈላጊው ሥፍራ በመላክ ይሰበሰብ እንደ ነበር የሚታወቅ ሲሆን፣ የሥራውን እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር፣ በገንዘብ አወጣጥና በአስተዳደር የነበረው ችግር በቀላሉ የሚገመት አልነበረም፡፡

ሆኖም የአስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በቀድሞ አብዮት በነበረው አስቸጋሪ ሁኔታ አቅሙ የፈቀደለትን ያህል የማይናቅ መጠነኛ የአስታቲስቲክስ ሥራዎችን አከናውኗል፡፡ በዚሁ መሠረት እስከ 1966 ድረስ በጽ/ቤቱ አማካይነት በዓይነት ከአሥራ አንድ በላይ የሆኑ ጥናቶች የተካሄዱ ሲሆን መጠቀስ ከሚገባቸው ዋና ዋናዎቹ የአንደኛና የሁለተኛ ዙር የብሔራዊ ናሙና ጥናት፣ ዓመታዊ የታላላቅ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ በከተሞች የዋጋዎች ጥናት፣ የቤ

... /4

ተሰብ ፍጆታ ጥናትና የዲምግራፊ የናሙና ጥናት ናቸው፡፡ ስለእነዚህ ጥናቶችም ሆነ በአጠቃላይ እስከ 1979 ድረስ በጽ/ቤቱ ስለተካሄዱት ጥናቶችና ቆጠራዎች ሁኔታ ወደ ኋላ በሪፖርቱ ውስጥ በጥናቶቹ ዓይነት በዝርዝር ይገለጻል፡፡

4. <u>በአብዮቱ ዓመታት የጽ/ቤቱ ድርጅታዊ አቋምና የአሠራር እንቅስቃሴዎች፣</u>

በ1966 የተቀጣጠለው የኢትዮጵያ አብዮት አያሌ መሠረታዊ ለውጦችን በማስከተሉና የቦሻሊስት ኅብረተሰብ ሥርዓት ጉዳና በመከተል በሁሉም የሥራ መስኮች አመቺ የአሠራር ዘዴዎችና ስልቶች በመቀየሳቸው፣ የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ከፍተኛ የሥራ እንቅስቃሴዎች መደረጋቸው ማስረዳ የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም፡፡

በተለይም የቦሻሊስት ሕግ ላይ የተመሠረቱ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የፓለቲካ መዋቅሮችን በመዘርጋት፣ የአገሪቷ የልማት እድገት በተስተካከለ ጽኑ መሠረት ተገንብቶ በአስተማማኝ ሁኔታ በማዕከላዊነት መርህ ለመምራት፣ በየወቅቱ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ቦሻሊስታዊ ፕላን ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ አብዮታዊ መንግሥር ነቀል እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ ከነዚሁ መካከል በ1971 በአዋጅ ቁጥር 156/1971 የተቋቋመው የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ አንዱ ነው፡፡ ጠቅላይ መምሪያው እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ክፍል መዋቅሩን በመዘርጋቱና በየደረጃው የፕላን አሠራር በመመሥረቱ፣ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ሂደትና በከነውን ወቅት ከተገኘው ልምድም ግንዛቤ ማድረግ እንደተቻለው፣ የሀገሪቷን የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ሁኔታ የሚገልጹ ወቅታዊ የሆኑ የአስታቲስቲካዊ መረጃዎች አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ከምንጊዜውም የበለጠ ጎልቶ በመገኘቱ አስታቲስቲክስ በአገሪቷ በሰፊው ሊታወቅ ችሏል፡፡

የአስታቲስቲክስን ተግባር እንዲያስፈጽም ቀደም ብሎ ተቋቁሞ የነበረው የአስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤትም በ1964 በአዋጅ የተሰጠውን ኀላፊነትና ተግባር በብቃት ለመወጣት በአብዮቱ ዓመታት የአገሪቷን የእድገት አቅጣጫዎችን በመከተል አቅሙ በፈቀደለት መጠን በርካታ ሥራዎችን አከናውኗል፣ አሁንም በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በጽ/ቤቱ የተከናወኑት ሥራዎች በዝርዝር ከመቅረባቸው በፊት በአሁኑ ወቅት ጽ/ቤቱ የሚገኝበትን ድርጅታዊ አቋም መግለጹ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

.../5

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ጽ/ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር በሚገባ በማመዛዘን፣ እስታቲስቲክስ በሲቪሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ወቅት ሊኖረው የሚገባውን ሚና በማገናዘብ፣ የጽ/ቤቱ ድርጅታዊ አቋም በየጊዜው እንዲሻሻል ጥረት ተደርጓል። ሆኖም አቋሙ ከሚጠበቀው ደረጃ ደርሷል ለማለት ባያስደፍርም በፊት ከነበረው ሁኔታ ተሻሽሏል። ለመጥቀስ ያህል ጽ/ቤቱ ሲመሠረት የነበሩት አራት ክፍሎች በ1965 በጽ/ቤቱ አራት መምሪያዎችና አሥራ ሦስት ዋና ክፍሎች ሲኖሩ እንደገና ከአብዮቱ ወዲህ በተደረገው ድርጅታዊ ለውጥ አንዱ መምሪያ ወደ ሌላ መ/ቤት ከተወሰደ በኋላ አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጓል። በዚሁ መሠረት ከ1973 ጀምሮ በመምሪያ ደረጃ ሊታዩ የሚገባቸው አምስት ማቀነባበሪያዎች፣ በዋና ክፍል ደረጃ መታየት ያለባቸው አሥራ አምስት የኤክስፐርት የቡድን ተጠሪዎችና ሌሎች እንደ አስተዳደር፣ ኦዲትና ኢንስፔክሽን የማተሚያና የመሳሰሉት ክፍሎች ይገኛሉ።

በአሁኑ ወቅት በጽ/ቤቱ የሚገኙት አምስቱ ማቀነባበሪያዎች

- የኢኮኖሚክ እስታቲስቲክስ ማቀነባበሪያ፣
- የሕዝብና ማኅበራዊ ጉዳይ እስታቲስቲክስ ማቀነባበሪያ፣
- የእርሻ እስታቲስቲክስ ማቀነባበሪያ፣
- የፕላንና ሜቶዶሎጂ አገልግሎት ማቀነባበሪያ፣
- የቴክኒክ አገልግሎት ማቀነባበሪያ፣

ሲሆኑ ጽ/ቤቱ የሚመራው በአንድ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ተጠሪነቱ ለማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ነው።

በበጀት፣በሰው ኃይልና በአሠራር ሁኔታዎችም ውሱን የነበረው የጽ/ቤቱ የሥራ ሁኔታ በየጊዜው እየሰፋ በመምጣቱ በ1971 በ14ቱም ክፍለ ሀገር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መቋቋማቸውና በመስክ ተግባር በኩል ያለው ቁጥጥር፣ በገንዘብና በሰው ኃይል አስተዳደር ይከሰት የነበረው ችግር በመጠኑም ቢሆን እየተሻሻለ መጥቷል።


ሌላው ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው በአሠራር የተደረገው ለውጥ ነው። በቀደም አብዮት እስታቲስቲካዊ ጥናቶች ሲካሄዱ የአንዱ ክፍለ ሀገር ሥራ እንደተጠናቀቀ ወደ ሌላ ክፍለ ሀገር በተራ በመሸጋገር ማከናወን ሲሆን ውጤቱም ከጊዜ አኳያ ክፍለ ሀገራትን ለማወዳደር የማያስችል እንደ ነበርና ነገር ግን ከ1973

ጀምሮ ሣይንሳዊ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ በተቀናጀና በተጠናከረ ሁኔታ ወቅ
ታዊ መረጃዎችን በሚፈለገው መንገድ ለመሰብሰብ በአሥራ ሁለት ክፍለ ሀገር በቂ
መረጃ ሰብሳቢዎችንና ተቆጣጣሪዎችን በመመደብ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የበላይ አስተ
ባባሪነት ጥናቶች እንዲካሄዱና ከሁሉም ቦታ በአንድ ወቅት መረጃዎች እንዲሰበሰቡ
በመደረጉ፣ የነበረው ችግር ከመቃለሉም በላይ በመረጃዎች ጥራትም ሆነ ብዛት እድ
ገት ታይቷል።

ምንም እንኳን በሶሻሊስት መርህ መንግሥታዊ መ/ቤቶችና ሕዝባዊ ድርጅቶች
በሁሉም የሥራ መስክ ግንባር ቀደም ኃላፊነት ያለባቸውና ለአስታቲስቲክስ ሥራዎች
አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር አጋዥ ገና ብዙ ቢጠበቅባቸውም እስከ ዛሬ ያበረከቱት
አስተዋጽኦ በተለይም በታሪካዊው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ እንዲሁም በብሔራዊ የተቀ
ናጀ የገጠር የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም የተደረገው ተሳትፍና ድጋፍ ሳይጠቀስ
መታለፍ የሌለበት አቢይ ድርጊት ነው።

ከዚህ በላይ በመጠኑም ቢሆን ስለ ጽ/ቤቱ ድርጅታዊ አቋምና የአሠራር
እንቅስቃሴዎችን በአጠቃላይ መልኩ ለማንጸባረቅ ተሞክሯል። ቀጥሎ ደግሞ ጽ/ቤቱ
ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ያካሄዳቸውን ጥናቶች በዓይነታቸው በመለየት፣ እንዲሁም
በጽ/ቤቱ የነበረው የበጀትና የሰው ኃይል እንቅስቃሴ ሁኔታ ይቀርባል።

## የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ድርጅታዊ መዋቅር



5. ከ1953 — 1979 በጽ/ቤቱ የተካሄዱ ጥናቶች፣

የአስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከተቋቋመበት ከ1953 ጀምሮ ብዛት ያላ ቸውን ጥናቶች አካሂዷል፡፡ እነዚህም ጥናቶች በዋና ዋና የጥናት ዓይነቶች ሲጠ ቃለሉ የሚከተሉት ናቸው፡፡

5.1 የግብርና አስታቲስቲክስ ጥናት /1973 — 1979/

5.2 የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት /1955፣ 1960፣ 1967፣ 1973/

5.3 በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደ የቤተሰብ ኢነርጂ ፍጆታ ጥናት /1971/72/

5.4 የአዲስ አበባ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ጥናት /1976/

5.5 የሕዝብና የቤቶች ጥናት/ 1953 — 1975/

5.6 የሰው ኃይል ጥናት / 1969፣ 1970፣ 1973፣ 1974/

5.7 የጤና፣ የአመጋገብና የአካባቢ ሁኔታ ጥናት / 1973፣ 1974፣ 1975/

5.8 ብሔራዊ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ / 1976/

5.9 ቋሚና መደበኛ የአስታቲስቲክስ ሥራ / 1955 — 1979/

5.9.1 የታሰሰቀ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት

5.9.2 የትራንስፖርትና መገናኛ አስታቲስቲክስ ጥናት

5.9.3 የዋጋዎች ጥናት

5.9.4 ዓመታዊ የአስታቲስቲክስ መጽሔት

ከዚህ በላይ የቀረቡት ዋና ዋና የጥናት ዓይነቶች ሲጤኑ የግብርና አስታ ቲስቲክስ ጥናት ከ1973 እስከ 1979 በየዓመቱ የተካሄደ መሆኑን፣ ከ5.2 እ ስከ 5.8 የተገለጹት የጥናት ዓይነቶች ደግሞ አንድ ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ በተ ለያዩ ጊዜያት መካሄዳቸውንና በ5.9 ሥር የተጠቀሱት ጥናቶች ከ1955 እስከ 1979 በቋሚነት የተካሄዱና በመካሄድ ላይ ያሉ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

...8

ስለእነዚህ የጥናት ዓይነቶች ዝርዝር ሁኔታ ቀጥለን እንመልከታለን፡፡

5.1 የግብርና እስታቲስቲክስ ጥናት / 1973 – 1979 /

በሀገራችን ካሉት ከፍለ ኢኮኖሚያች መካከል ሰውጭ ንግድ፣ ለመተዳደሪያ የሥራ መስክ በማስገኘትና በሌሎችም ተግባራት የላቀ ድርሻ ያለውና በቅድመ አብዮትም ሆነ በድህረ አብዮት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከፍተኛውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ያለው የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

ይህን የኢኮኖሚ ዘርፍ በአስተማማኝና በበቂ ሁኔታ ሊገልጹ የሚችሉ ወቅታዊ የሆኑ የግብርና እስታቲስቲክስ መረጃዎች በየጊዜው መገኘት እንዳለባቸው የሚታመን ሲሆን የተገኙት መረጃዎች በዘርፉም ሆነ በብሔራዊ ደረጃ ጠቃሚነታቸው ወይም አስ ፈላጊነታቸው አያጠያይቅም፡፡

ይሁንና ሕዝባዊ አብዮት በ1966 ከመቀጣጠሉ በፊት ይህን ክፍለ ኢኮኖሚ የሚመለከት እስታቲስቲካዊ መረጃዎች በተበታተነ ሁኔታ በአንዳንድ መ/ቤቶች ይሰበ ሰብ እንደነበር ቢታወቅ፣ በነበረው ሁኔታ አንጻር ሲታይ በመጠኑም ቢሆን በተሻለ መንገድ ይከናወን የነበረው በግብርና ሚኒስቴር ሲሆን ከአብዮቱም በኋላ እስከ 1972 ድረስ በዚሁ መ/ቤት የመረጃ አሰባሰቡ ተግባር ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ ከ1972 በኋላ ግን ይኸኑ ዘርፍ በሚመለከት ሰፋ ባለው ሁኔታ በእስታቲስቲክስ ጠ/ጽ/ቤት አማካኝነት በየዓመቱ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የግብርናው ዘርፍ ለሀገራችን ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተ ዋጽኦ ያለው በመሆኑ፣ አብዮታዊ መንግሥት በየጊዜው በሚያወጣቸው መመሪያዎች ይህ ዘርፍ ትኩረት እንዲያገኝ በመደረጉ በእስታቲስቲክስ ተግባርም ይህን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ አስተማማኝና ወቅታዊ የሆኑ የግብርና መረጃዎችን ለማስገኘት እንዲቻል ከ1972 ጀምሮ አስፈላጊው እርምጃ ተወስዷል፡፡

1ኛ/ በግብርና ሚኒስቴር ሥር የነበረው የእርሻ እስታቲስቲክስ ንዑስ ክፍል ከነበረው የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ጋር ወደ እስታቲስቲክስ ጠ/ጽ/ቤት እንዲዛወር መደረጉ፣

2ኛ/ በእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት ያለውን የግብርና እስታቲስቲ ክስ ንዑስ ክፍል አቋሙ ተሻሽሎ ወደ ማቀነባበሪያ ክፍ ማለቱ፣

3ኛ/ በ1972 በተባበሩት መንግሥታት የምግብና እርሻ ድርጅት(FAO) ጋር የእርዳታና የትብብር ስምምነት በማድረግ "ብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም" በሚል ስም አንድ ፕሮጀክት መቋቋሙ፣

4ኛ/ ከ1973 እስከ 1979 ድረስ በሀገር አቀፍና በክፍለ ሀገር ደረጃ ሲያገለግል የሚችል የግብርና እስታቲስቲክስ መረጃ በተ ጠናከረ መልክ በየዓመቱ እንዲሰበሰብ መደረጉ መጠቀስ ከሚገ ባቸው እርምጃዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በግብርና ዘርፍ የተደረገውን የሥራ እንቅስቃሴና ያለበትን ሁኔታ በሀገር አቀፍና በክፍለ ሀገር እረጃ ለመገምገም የሚያስችል እስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለመ ሰብሰብ ከ1973 ጀምሮ በመካሄድ ላይ ባለው የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም አማካይነት የእርሻ ናሙና ጥናትና የሰብል ትንበያ ጥናት በመባል የሚታወቁ ሁለት ግብርና ነክ ጥናቶች በ12 ክፍለ ሀገር ሌር ትራንና ትግራይን አይጨምርም/ በሣይንሳዊ ዘዴ በተመረጡ 500 ገበሬ ማኅበራትና 12,500 የገበሬ ቤተሰብን በሚሸፍን ሁኔታ በየዓመቱ ሲካሄድ ቆይቶ ይኸኑ ጥናት እንደገና በማስፋት በ1978/79 750 ገበሬ ማኅበራት እንዲሸፈኑ ተደርጓል። የእነዚህ ጥናቶች ዓላማና የሚሰበስቡት የመረጃ ዓይነቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል።

### 5.1.1 የእርሻ ናሙና ጥናት

የእርሻ ናሙና ጥናት የሚሸፍነው የግል ባለይዞታዎችንና የሕብረት እርሻዎችን በሚመለከት ሲሆን ጥናቱም በዋናው መኸርና በበልግ ወቅት በሀገሪቷ በግብርና ነክ ያለውን እንቅስቃሴ የሚያመለክት መረጃ በማስገኘት የሚከተሉት ዓላማዎች ከግብ እንዲ ደርሱ ታስቢ በማድረግ ነው። እነዚህም ዓላማዎች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- በሀገሪቷ የተመረተውን የምርት መጠንና የታረሰውን መሬት ስፋት ለመገምገም፣
- ስለማዳበሪያ፣ ስለምርጥ ዘር፣ ስለፀረ—ሰብል ተባይ ማጥፊያ መድኃኒትና ስለመስኖ ሥራ የገበሬውን አጠቃቀም ልምድ ለማወቅ፣
- የቤት እንስሳትን ብዛት በዓይነቱ ለማወቅ፣

.../10

- የገብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ለአጠቃላይ የሀገር ሀብት ያለውን ድርሻ ለመገምገም፣
- በክፍለ ሀገር ደረጃ ያለውን የምርት ሁኔታ ለማነጻጸር፣
- በየዓመቱ ያለውን የምርትና የታረሰ መሬት ስፋት ለውጥን ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለማስገኘት ነው። መረጃውም በክፍለ ኢኮኖሚው ለሚዘጋጁት የልማት ዕቅዶችና የፖሊሲ ውሳኔዎች እንደሚያገለግል ይታመናል።

በዚህ ጥናት ከሁለቱም በለይዘታዎች የሚሰበሰቡት ዋና ዋናዎቹ የመረጃ ዓይነቶችም፡—

- የታረሰ መሬት ስፋት በሰብል ዓይነት
- ጥቅም ላይ የዋለ የማዳበሪያ ዓይነትና መጠን
- የዘር ዓይነት አጠቃቀም ልምድ
- የመስኖ ሥራ አጠቃቀም ልምድ
- የፀረ—ሰብል ተባይ ማጥፊያ መድኃኒት አጠቃቀም ልምድ
- የሰብል መበላሸት ምክንያቶችና የጉዳቱ መጠን /ከመቶ/
- የቤት እንስሳት ብዛት በዓይነት፣ በዕድሜና በጾታ
- ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛት

ሲሆኑ ከአምራቾች የሕብረት ሥራ ማኅበራት የሚከተሉት ተጨማሪ የመረጃ ዓይነቶች ይሰበሰባሉ።

- ማኅበሩ ስሰለበት ደረጃ
- [illegible]ከፒታልና የአባላት ብዛት
- የእርሻ መሣሪያዎች ዓይነትና ብዛት

5.1.2 <u>የሰብል ትንበያ ጥናት</u>

የሰብል ትንበያ ጥናት ዋና ዓላማ የዓመቱ ሰብል አጨዳ ከመድረሱ በፊት ሊመረት የሚችለውን የምርት መጠን ሣይንሳዊ በሆነ መንገድ አስቀድሞ ለመገመትና ከምርት አኳያ የሚፈለገውን ገንዘብ ለማግኘት የሚያስችል መረጃ ለማዘጋጀት ነው። ይህ መረጃ ካለው የሕዝብ ብዛት ጋር ተነጻጽሮ ለምግብ ፍጆታ የሚውል በቂ ወይም የሚያንስ መሆኑን በቅድሚያ በመጠቆም ተገቢና ወቅታዊ የሆነ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ነው።

.../11

በዚህ ጥናት የሚሰበሰበው የመረጃ ዓይነት፡—

— የታረሰ መሬት ስፋት በሰብል ዓይነት
— የሚጠበቀው የምርት መጠን ሰውጥ ከተሰመደው የሰብል ዘመን ምርት ጋር ሲወዳደር ከመቶ ምን ያህል እንደሆነ የሚገልጽ ይሆናል፡፡

ከጥናቶቹ የተገኘው ውጤትም በአራት የሪፖርቶች ዓይነት ተጠቃሎ በየጊዜው ወጥቷል፡፡

5.2 የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት/ 1955 —1973/

የቤተሰብ ፍጆታና ወጪ ጥናት ከአብዮቱ በፊትም ሆነ ከአብዮቱ በኋላ በተለያዩ ዓመታት በገጠርና በከተማ የተካሄደ ሲሆን የጥናቱ ይዘትና ስፋት ማለትም የጥናቱ ዓላማ፣ የተሰበሰቡ የመረጃ ዓይነቶች፣ የአሠራር ዘዴዎች፣ በጥናቱ የተሸፈኑ የቤተሰብ ብዛትና የመጠይቁ አንደየዓመቱ የሚለያይ መሆኑ በቅድሚያ እንዲታወቅ ያስፈልጋል፡፡ ስለሁኔታው ግንዛቤ ለመስጠት በመጀመሪያ ከተካሄደው ጥናት ጀምሮ እንደ ጥናቱ ቅደም ተከተል ከዚህ በታች የቀረበ ስለሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

5.2.1 የአዲስ አበባ ከተማ የቤተሰብ በጀት ጥናት — 1955

በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ 600 ያህል ቤተሰቦች ላይ በመመሥረት የቤተሰብ ገቢና ፍጆታ ሁኔታን የሚገልጽ መረጃ ለማስገኘት በ1955 ጥናት ተካሄዷል፡፡ የጥናቱም ዓላማ የአዲስ አበባ የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለማዘጋጀት እንደ ነበር ሲታወቅ የጥናቱም ውጤት በልዩ ልዩ ምክንያት በይፋ ታትሞ ያልወጣ ቢሆንም ለተጠቀሰው ዓላማ መሠረት ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

5.2.2 በገጠር የቤተሰብ ወጪና ፍጆታ ጥናት — 1960

የገጠር የቤተሰብ ወጪና ፍጆታ ጥናት ለመጀመሪያ ጊዜ በ1960 ከ12 ክፍለ ሀገር /ባሌና ኤርትራን አይጨምርም/ በተመረጡ ቤተሰቦች ላይ እንዲካሄድ የተደረገ ሲሆን የጥናቱም ዓላማ የነፍስ ወከፍ የፍጆታ መጠን ለማወቅና የገጠሩ ሕዝብ ያለበትን የኑሮ ደረጃ ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለማግኘት፣ እንዲሁም የብሔራዊ ሀብት ነክ አኀታቲስቲክስን ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ መረጃ ለማስገኘት ነበር፡፡ ከዚሁ አኳያ ቤተሰቦች ለምግብ፣ ለመጠጥ፣ ለልብስና ለመጠለያ

የሚያወጡት ወጪና መጠን የሚመለከቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

ይህ ጥናት 12ቱን ክፍለ ሀገር በሚሸፍን ሁኔታ ይካሄድ እንጂ በአንድ ወቅት የተካሄደ ባይሆን የአንዱ ክፍለ ሀገር ጥናት ሲያልቅ ወደ ሌላ ክፍለ ሀገር በመሸጋገር የተከናወነ በመሆኑ ክፍለ ሀገራትን ለማወዳደር የሚያስችል ጥናት እንዳልሆነ ግልጽ ቢሆንም የጥናቱ ውጤት በሪፖርት መልክ ወጥቷል።

## 5.2.3 በአዲስ አበባ የቤተሰብ ወጪና ፍጆታ ጥናት — 1960

በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደው የወጪና ፍጆታ ጥናት በገጠር በዚህ መስክ ከተካሄደው ጥናት ጋር በዓላማ በመረጃ ዓይነት ተመሳሳይነት ቢኖረው የነበረው ለውጥ ደግሞ የቤተሰብ አመራረጥ ሲሆን በአዲስ አበባ ጥናቱ የተካሄደው እስከ 100 ሠራተኞች ከነበሯቸው ትልቅ ድርጅቶች ውስጥ በወር እስከ ብር 300 ደሞዝ የሚያገኙ ሠራተኞች ካሉባቸው ቤተሰቦች በተመረጡ 249 ቤተሰቦች ላይ ነበር። የጥናቱም ውጤት በሪፖርት መልክ ወጥቷል።

## 5.2.4 በከተሞች የቤተሰብ ፍጆታ ጥናት — 1967

ከአብዮቱ በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ብቻ አተኩሮ የነበረው የቤተሰብ ፍጆታ ጥናት በ1967 በስፋት እንዲካሄድ በተደረገው ጥረት አዲስ አበባን ጨምሮ በተመረጡ 30 ከተሞች ተካሄዷል። ጥናቱም በደሞዝ የሚተዳደር የቤተሰብ አባል ካለባቸው ቤተሰቦች ውስጥ የተመረጡትን 2,332 ያህል ቤተሰቦችን ያቀፈ ሲሆን የተካሄደውም ከሚከተሉት ዓላማዎች አኳያ ታይቶ ነበር።

— አንድ ቤተሰብ በተወሰነ ወቅት ለተለያየ የወጪ ዓይነት የሚያስፈልገውን ወጪ ለማስላት፣
— በተለያየ የገቢ መጠን ያለውን የፍጆታ መጠን ለማወቅ፣
— የዋጋ ፖሊሲ በፍጆታ ላይ ያስከተለውን ለውጥ ለመገምገም፣
— የአንዱን ክልል የአኗኗር ደረጃ ከሌላው ክልል የአኗኗር ደረጃ ጋር ለማነጻጸር፣
— የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ /ኢንዴክስ/ ለማዘጋጀት።

ከዚሁ አንጻር ቤተሰቦች ለፍጆታ ያወጡት ወጪ፣ ያገኙት ገቢና የመሰሱት የመረጃ ዓይነቶች ተሰብስበዋል፡፡ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት የአዲስ አበባ፣ የአሥመራና የድሬዳዋ ከተሞች መረጃ በሪፖርት መልክ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች የተ ሠራጨ ሲሆን ለሌሎች ከተሞች ግን መሠረታዊ የሆኑ መረጃዎች በሠንጠረዥ መልክ ተዘ ጋጅተዋል፡፡

## 5.2.5 በገጠር የቤተሰብ ፍጆታ ጥናት — 1973

ይህ ጥናት ቀደም ሲል ከአብዮቱ በፊት ለየት ባለ አሠራር መካሄዱ ቢታወ ቅም ከአብዮታችን ፍንዳታ ወዲህ በተለይም ከ1971 ጀምሮ ከፍለ ኢኮኖሚያችንና ማኅበራዊ ዘርፎችን በዕቅድ ለመምራት አመቺ የአሠራር ሁኔታዎች በመፈጠራቸው በገ ጠር የቤተሰብ ፍጆታ ጥኛትን በስፋትና በጥልቀት ማካሄድ እንደሚቻልና ውጤቱም የማ ኅበራዊና የኢኮኖሚ ዕቅዶችን ለማዘጋጀት እንዲሁም የፖሊሲ ውሳኔዎችን ለማውጣት እንደሚረዳ ታምኖበት በ1973/74 ተካሂዷል፡፡

ይህ በ1973/74 ለአንድ ዓመት ጊዜ በአራት ዙር የተካሄደው ጥናት ከ12 ክፍላተ ሀገር /ኤርትራንና ትግራይን አይጨምርም/ የተመረጡ 500 ያህል ገበሬ ማኅ በራትና 12 ሺህ ያህል ቤተሰቦችን ያቀፈ ሲሆን የጥናቱ ዓላማና የተሰበሰቡ የመረጃ ዓይነቶችም ሰፋትና ጥልቀት እንዳገኙ መገመት አያዳግትም፡፡

የገጠሩን ሕዝብ የገቢ፣ የፍጆታና የወጪ መጠን ማጥናት ያስፈለገበትን ዋና ዋናዎቹን ዓለማዎች መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

1ኛ/ የገጠሩ ሕዝብ የሚመገበውንና የሚጠጣውን የምግብና የመጠጥ ፍጆታ መጠንና ዓይነት፣ እንዲሁም ለልብስ፣ ለኢነርጂ፣ ለቋሚ የቤት ዕቃና ለመሰሰሉት የወጣውን ወጪ ለመገምገም፣

2ኛ/ የአንዱ ክፍለ ሀገር የገጠር ነዋሪዎች ያሉበትን የኑሮ ደረጃ ከሌላው ክፍለ ሀገር ገጠር ነዋሪዎች የኑሮ ደረጃ ጋር ለማወዳደር፣

3ኛ/ ገበይትና ፍጆታን የሚመለከት ምርምር ለማካሄድና አቅርቦትን ለማሻሻል፣

4ኛ/ ገጠሩን በሚመለከት የኑሮ ሁኔታ መመዘኛ /ኢንዴክስ/
ለማስላት፣

5ኛ/ የሀገር ሀብት መጠንን የሚያመለክት መረጃ አካል በመሆኑ
ለዚህ ተግባር የሚሰበሰበውን መረጃ ጥራቱን ለማሻሻል
ያገለግላል።

በተካሄደው ጥናት የተሰበሰቡት ዋና ዋና የመረጃ ዓይነቶች፦

- የቤተሰብ አባላት ዝርዝር ሁኔታ፣
- የቤተሰብ ፍጆታ ዓይነት፣ መጠንና ጠቅላላ ዋጋ፣
- ለቤተሰብ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች ዓይነት፣ መጠንና ጠቅላላ ዋጋ፣
- ለቤተሰቡ እንደ ወጪ የማይታሰቡ ክፍያዎች /አስቀብ፣ ተቀራጭ፣ መጽዋት፣... ወዘተ/
- የቤተሰብ የንግድ ወይም የማምረቻ ድርጅቶች ወጪ፣
- የቤተሰብ ገቢ ዓይነት፣ መጠንና ጠቅላላ ዋጋና የመሳሰሉት ናቸው።

5.3 <u>በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደ የቤተሰብ ኢነርጂ ፍጆታ ጥናት – 1971/72</u>

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ በሐምሌ ወር 1971 እና በየካቲት ወር
1972 በሁለት ዙር የተካሄደ ሲሆን ለጥናቱ መሠረት የሆኑት የተመረጡት 500
ያህል ቤተሰቦች ነበሩ።

የኢነርጂ ፍጆታ ጥናት ዋና ዓላማውም ቤተሰቦች የሚጠቀሙበትን ኢነርጂ
ፍጆታ ዓይነት፣ መጠንና ለፍጆታ የሚያወጡትን ወጪ በማወቅ አማራጭ የኢነርጂ ምን
ጮች ለማቅረብ የሚያስችል ፕሮግራም ለማውጣትና የኢነርጂ ምንጮችን በሚመለከት
ፖሊሲ ለመቀየስ የሚረዳ መረጃ ለማስገኘት ነው። የተሰበሰበውም መረጃ ቤተሰቦች
ለእንጨት፣ ለከሰል፣ ለኤሌክትሪክ፣ ለመብራትና ለመሳሰሉት የኢነርጂ ምንጮች ያወ
ጡትን ወጪና የተጠቀሙትን መጠን የሚመለከት ነበር። የዚህ ጥናት ውጤት በሪፖ
ርት መልክ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

.../15

## 5.4 የአዲስ አበበ ኢኮኖሚ ድርጅቶች ጥናት — 1976

ይህ ጥናት በአዲስ አበበ ከተማ በ1976 የተካሄደ ሲሆን የጥናቶ ዓላማ ዎች የኢኮኖሚ ድርጅቶች ብዛትና የንግድ አዘረጋግ አውታር መዘበትና አለመዘበቶን ለማወቅ፣ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ብዛት ከሚመረተው ጥሬ ዕቃ ምርት ጋር የተገናዘበ መሆኑን ለመገምገም፣ በከተማው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ መንግሥታዊና ሕዝበዊ ድርጅቶች ያሳቸውን ድርሻ ለማወቅ፣ የንግድ ፈቃድ አሰጣጥ መልክና ሥርዓት ለማስ ያዝ፣ በልዩ ልዩ ኢኮኖሚ ዘርፎች የተሰማሩትን ድርጅቶች በመለየት መዝገብ ለማዘ ጋጀት፣ የንግድ ፈቃድ ከመስጠትና ከማደስ አገልገሎት የሚገኘው የመንግሥት ገቢ በወቅቶ መሰብሰቡን ለማረጋገጥና ይህን መሰከ በማመለከት ወደፊት ለሚደረጉ ጥናቶች መሠረት መጣል ናቸው።

በጥናቶ የተሰበሰቡ የመረጃ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው:—

- የኢኮኖሚ ድርጅቶች አድራሻና ሕጋዊ አቋም፣
- ካፒታል
- ስለንግድ ፈቃድ ሁኔታ
- የድርጅቶ ዓይነት
- ለንግድ ሥራ የሚያስፈልገውን ሸቀጥ ወይም ጥሬ ዕቃ የሚያገኝበት ምንጭ
- ድርጅቶ ከሚያመርታቸው፣ ከሚገዛቸውና ከሚሸጣቸው ወይም ከሚያቀርባቸው አገልገሎቶች ዋና ዋናዎቹ
- የድርጅቶ ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች ብዛት
- የድርጅቶ ባለቤት አድራሻ
- የቤተሰቡ ገቢ ሁኔታ
- ድርጅቶ ሥራውን የሚያካሄድበት ቤት ይዞታ... ወዘተ.

## 5.5 የሕዝበና የቤቶች ጥናት / 1953 — 1975 /

ማንኛውም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የሥራ እንቅስቃሴ በማዕከለዊ ዕቅድ እንዲ መራ፣ከትትልና ቁጥጥር እንዲደረግበት አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት፣ ኋሰቀር አሠራ ሮችን በማስወገድ የሰፊውን ሕዝብ የኑሮና የበሕል ደረጃ በሚያስተማምን ሁኔታ ለማ ሳደግና ለከፍተኛ የእድገት ደረጃ ለማብቃት መሆኑ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ሕግ ያመለከታል።

ከዚሁ አኳያ መጠን ያለበት የአንድ አገር የልማት እድገት ከአገሪቷ የሕዝብ እድገት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን በብሔራዊ ደረጃ ለመከታተልና ለመቆጣጠር፣ ብሎም ሕዝቡን በተመለከተ ቢሔራዊ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት የሕዝብን ብዛትና ሁኔታ የግድ የማወቁ አስፈላጊነት ነው፡፡

ስለሕዝብና ቤቶች ሁኔታዎችን የሚገልጹ አስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማግኘት በተለያዩ ጊዜያት ጥናቶች ተካሄደዋል፡፡

እነዚህም ጥናቶች፡—

1ኛ/ ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ጋር በመተባበር የአዲስ አበባ ከተማ የሕዝብ ቆጠራዎች በ1953 እና በ1959፣

2ኛ/ የአንደኛው ዙር ብሔራዊ የናሙና ጥናት በ1956፣

3ኛ/ ከአሥመራ ማዘጋጃ ቤት ጋር በመተባበር ከተማውን የሚያጠቃልል የሕዝብና ቤት ቆጠራ በ1960፣

4ኛ/ የሁለተኛው ዙር ብሔራዊ የናሙና ጥናት በ1961፣

5ኛ/ ከከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ ከተማ የቤቶች ምዝገባና የዳሰሳ ጥናት በ1970፣

6ኛ/ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ከገጠር የአርሻ ናሙና ጥናት ጋር ተቀናጅቶ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት በ1971፣

7ኛ/ ብሔራዊ የተቀናጀ የገጠር ስርቬይ ፕሮግራም አካል በመሆኑ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት በ1973/74፣ እንዲሁም በ1975 በገጠር የቫይታል ምዝገባ ሙከራ ጥናት፣

ሲሆኑ የጥናቶቹም ዓላማዎች ቀጥሎ በተገለጸው መሠረት ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡

— የአገሪቱን የሕዝብ ብዛት በጾታና በዕድሜ ለማወቅ፣
— የሕዝቡን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባህርያት የሚገልጹ መረጃዎችን ለማግኘት፣
— የቤቶችን ብዛትና ዝርዝር ሁኔታዎች ለማወቅ፣
— የሕዝቡን የልደት፣ የሞትና የፍልሰት ሁኔታ በማወቅ የሕዝቡን እድገት ለመገምገም፣

— ብሔራዊ ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ ሕዝብና ቤቶች ነክ ዝርዝር መረጃዎችን ለማግኘት፡፡

ከላይ በተገለጹት ጥናቶች አማካይነት ስለተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት በሚመለከት የተለያዩ ሪፖርቶች የወጡ ቢሆንም በአሠራር ከነበሩት ችግሮች በተለይም የአንደኛውና የሁለተኛው ዙር ብሔራዊ የናሙና ጥናቶች ቢካሄዱ መ/ቤቱ በነበረው አነስተኛ አቅም ምክንያት የአንዱ ክፍለ ሀገር ሥራ ቢጠናቀቅ ወደ ሌላ ክፍለ ሀገር በመቀጠል መከናወኑ መጠቀስ ያለበት ነው፡፡

5.6 <u>የሰው ኃይል ጥናት /1969 — 1974</u>/

በብሔራዊ ደረጃም ሆነ በየሥራው ዘርፍ የሚዘጋጁትን የልማት ፕሮግራሞችንና የአሠራር ዘዴዎችን በሣይንሳዊ መንገድ በመጠቀም ተግባራዊ ለማድረግ፣ በሀገሪቱ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ በማዋልና ለሚፈለገው የእድገት ግብ በማድረስ ረገድ የሰው ኃይል የሚጫወተው ሚና ከፍተኛና ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡

ከአብዮቱ በፊት የሰው ኃይልን በሚመለከት የዲሞግራፊ ወይም የሕዝብ ጥናቶች ሲካሄዱ አንዳንድ መረጃዎች አብረው እንዲሰበሰቡ ከመደረጉ ሌላ እራሱን የቻለ ጥናት አልተካሄደም ነበር፡፡ ሆኖም በአብዮቱ ዓመታት ለዚሁ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶት አገሪቱ ያሏትን የሠራተኞች ብዛትና የሥራ ሁኔታዎችን ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለማስገኘት አንዳንድ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ እነዚህም፡—

— በአዲስ አበባ ከተማ የሰው ኃይልና የቤቶች ጥናት በ1969፣
— የ17 ትላልቅ ከተሞች የሰው ኃይልና የቤቶች የናሙና ጥናት በ1970፣
— በገጠር የሰው ኃይል ጥናት በ1973/74 /ብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም አካል በመሆን/ የተካሄዱት ናቸው፡፡

በእነዚሁ ጥናቶች የተሰበሰቡት መረጃዎችም ዋና ዋናዎቹ የዲሞግራፊና የማኅበራዊ ነክ መረጃዎች፣ በሥራ በመሰማራት ዕድሜ ክልል ላለው የሕዝብ ክፍል ዝርዝር የኢኮኖሚ መረጃዎች ማለትም የተሠማሩበት የሥራና የኢንዱስትሪ ዓይነት፣ ስለሠሩበት ጊዜ፣ ካልሠሩ ያልሠሩበት ምክንያት፣ ከመደበኛ ሥራቸው ሌላ ተጨማሪ ሥራ እንዳላቸውና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

5.7 <u>የጤና፣ የአመጋገብና የአካባቢ ሁኔታ ጥናቶች /1973 – 1975/</u>

በ1974 እና በ1975 በገጠር የጤናና የአመጋገብ ጥናቶች ተካሄደዋል፡፡ የእነዚህ ጥናቶች አስፈላጊነት የገጠሩ ሕዝብ በጤንነትና በአመጋገብ ሁኔታዎች ያለበትን ደረጃ ለመገምገም የሚያስችል መረጃ መሰብሰብ ሲሆን ከጥናቶቹ የሚገኘው ውጤት የአመጋገብና የጤንነት ሁኔታዎችን ለማሻሻል ለሚዘጋጁ ዕቅዶች፣ ለሚቀየሱ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች መሠረት በመሆን የሚያገለግል መሆኑ ስለሚታመን ነው፡፡

በእነዚህ መስኮች የተሰበሰቡት መረጃዎችም፡—

— ስለሕዝብ የዲሞግራፊና የማኅበራዊ ሁኔታዎች የሚያመለከቱ መጠነኛ መረጃዎች፣
— ስለሕመምና ሞት ሁኔታ፣
— በአደጋ ወይም በተመሳሳይ ምክንያቶች ስለሚደርሱ ጉዳቶች፣
— ስለሕክምና መሸትና ማግኘት፣
— ስለወሊድና አቀራረቦች፣
— ስለመሠረታዊ ገለጋሎቶችና ልምዶች መኖር፣
— የቤተሰብ አበላት የአመጋገብ ሁኔታዎች፣
— ስለሕፃናት ሁኔታዎች፣

ቀና ቀናዎቹ ናቸው፡፡

እንደዚሁም በ1973 የተካሄደው የገጠር የአካባቢ ሁኔታ ጥናት በየአካባቢው ያለውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስርጭቶችን ማለትም የትራንስፖርትና መገናኛ፣ የትምህርት የጤና... ወዘተ. አገልግሎቶችን፣ የመጠጥ ውሃ፣ የማገዶ እንጨትና ሌሎችም የተፈጥሮ ሀብቶች መኖራቸውን፣ የአኗኗር ሁኔታ፣ በገብርና ዘርፍ ያሉትን አገልግሎቶችና በአካባቢ የሚገኙትን የጎጆ ኢንዱስትሪዎችን ሁኔታ ለማወቅና ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለማስገኘት የታሰበ ነበር፡፡

.../19

## 5.8 ብሔራዊ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ /1976/

የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ በብሔራዊ ፕሮግራም አማካይነት መከናወን ያለበት፣ ከፍተኛ ዝግጅትን፣ ወጪንና የሰው ኃይልን የሚጠይቅ ትልቅ ተግባር በመሆኑ ቢያንስ በአሥር ዓመት አንዴ መካሄድ እንደሚኖርበት የሚታወቅ ነው፡፡ ሆኖም አገራችን አንድም ጊዜ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ካላካሄዱት ሦስት የአፍሪካ አገሮች አንዷ እንደነበረች አይዘነጋም፡፡

ይህ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ተግባር አብዮታችን ከተቀጣጠለ ወዲህ መከናወን ያለበት አቢይ ጉዳይ ሆኖ በመገኘቱ የሚያስፈልጉት መሠረታዊና ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እንዲጀመሩ ተደርጓል፡፡ ከሚያስፈልጉት ቅድመ ዝግጅቶች አንዱ የካርታ ሥራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የካርታ ሥራ ለቆጠራ አመቺ አሠራሮችን ለመፍጠር የአገሪቷን የመልክአ ምድር አቀማመጥ ከዝቅተኛው የአስተዳደር ወሰን ጋር በማዛመድ ቆጠራ የሚካሄድበትን የቦታ ክልል በቆጠራና መቆጣጠሪያ ክልሎች መሸንሸን የሚያጠቃልል ሲሆን ለቆጠራ ሥራ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል፣ በጀትና ሌሎች ቁሳቁሶችን በቅድሚያ ለመገመት ያስችላል፡፡

በመሆኑም በጽ/ቤቱ በቅድመ አብዮት ያልነበረው የካርቶግራፊ አገልግሎት በ1967 እንዲቋቋም በመደረጉና በየጊዜው ለማጠናከር የተደረገው ጥረት ቀጥሎ በ1973 ከተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ጉዳይ ፈንድ ከፍተኛ የገንዘብ፣ የቴክኒክና የቁሳቁስ እርዳታ በመገኘቱ 12ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ቁጥራቸው ከ600 በላይ የሆኑ ሠራተኞችን በኮንትራት በመቅጠር፣ በሙያው በማሠልጠንና በማሰማራት በ1973 የተጀመረው የካርታ ሥራ ሚያዝያ 1976 ሊጠናቀቅ ችሏል፡፡

የካርታ ሥራና መሰል ቅድመ ዝግጅቶች እንደተጠናቀቀ የሚቀጥለው ተግባር ቆጠራውን ማካሄድ ነበር፡፡ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራን ለማካሄድ ከመንግሥት የተፈቀደው በጀትና የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ከፍተኛ በመሆኑ ሥራውን በየደረጃው ጥራት ባለው አኳኋን በማንቀሳቀስ ለማስተባበር፣ ለመምራትና ለመቆጣጠር ብሔራዊ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 252/1976 ተቋቁሞ መዋቅሩን እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ክልል በመዘርጋት፣ ወደ 60 ሺህ የሚጠጉ መረጃ ሰብሳቢዎችንና የበላይ የመስክ ተቆጣጣሪዎችን በማሠልጠንና በማሰማራት፣ በዚህ ሥራ በዓይነቱ የመጀመሪያ በመሆን የተመዘገበው የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ግንቦት 1976 በአጥጋቢ ሁኔታ ተካሄዷል፡፡ በአገሪቷ የታሪክ ማኅደርም ለመመዝገብ በቅቷል፡፡

... /20

ቀጠሪው በመካሄዱ ምክንያት የተሰበሰቡት መረጃዎች ጠቅለል ባለ ሁኔታ ሲታይ እንደሚከተለው ነው፡፡

1ኛ/ ስለሕዝብ ብዛት በጾታና በዕድሜ፣

2ኛ/ ስለሕዝቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣

3ኛ/ የልደት፣ የሞትና የፍልሰት መጠን፣

4ኛ/ ስለመኖሪያ ቤቶች ሁኔታ፡፡

እነዚህ መረጃዎች በብሔራዊም ሆነ በክልል ደረጃ ለልዩ ልዩ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ዝግጅት ከፍተኛ ጥቅም ከመስጠታቸውም ሌላ ወደፊት በስፋትና በጥራት ለሚካሄዱ የስታቲስቲክስ ጥናቶች መሠረት በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

## 5.9 ቋሚና መደበኛ የስታቲስቲክስ ሥራ /1955 – 1979/

በዚህ ርዕስ ሥር የሚጠቃለሉት ጥናቶች የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ የትራንስፖርትና መገናኛ፣ የዋጋዎች ጥናቶች፣ እነዚህንና ሌሎች የተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚገልጹ ልዩ ልዩ እስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የያዘ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ናቸው፡፡

እነዚህን ጥናቶች በተመለከተ ዝርዝር የሥራ እንቅስቃሴን ማቅረቡ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

### 5.9.1 የታሰሰቅ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት

የዚህ ጥናት ዓላማ በኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚካሄደውን ዝርዝር የሥራ እንቅስቃሴ በማወቅ ለሀገር ሀብት ውጤት ያላቸውን ድርሻ ለመገምገም፣ በየጊዜው የሚከሰተውን ለውጥ በመረዳት ብሔራዊ የልማት ፕላን ለማዘጋጀት፣ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት የታሰሰቅ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የሚሸፍነው 10 እና በላይ ሠራተኞች ያሏቸውን ኢንዱስትሪዎች በሙሉ ሲሆን ይህ ጥናት ከ1955 ጀምሮ በየዓመቱ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ከአብዮቱ በፊት እነዚህን ኢንዱስትሪዎች የሚመለከት መረጃ በአጠቃላይ መልኩ በዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ውስጥ እየታተመ ይወጣ እንደ ነበር ሲታወቅ አብዮቱ ባስገኘው ከፍተኛ ድል ትላልቅ ኢንዱ

ስትሪያች በመንግሥት ይዞታ ሥር በመሆናቸው የመንግሥትና የግል ይዞታን በመለ
የት የአሠራሩንም ዝርዝር መረጃዎችን ማውጣት የተቻለ ከመሆኑም ሌላ ከ1968
ጀምሮ በተጠማሪ ለዚሁ ተግባር የተለየ መጽሔት እየታተመ ይወጣል።

ይህ ጥናት በየዓመቱ በቋሚነት የሚካሄድ ሲሆን የሚሰበስቡት የመረጃ ዓይነቶች፤

- የፋብሪካ ብዛትና ሕጋዊ አቋም
- የሠራተኞች ብዛትና ደምዝ
- የምርትና የሽያጭ መጠንና ጠቅላላ ዋጋ
- የጥሬ ዕቃ ፍጆታ በዓይነት
- የልዩ ልዩ ወጪዎች ዋጋ
- የማይንቀሳቀስ ንብረት
- የመዋዕለ ንዋይ ወጪና የመሳሰሉት ናቸው።

5.9.2 <u>የትራንስፖርትና መገናኛ እስታቲስቲክስ</u>

ለሀገር እድገት የሚደረገውን አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ በተገቢው ሁኔታ ለማከናወንና ለማስተዳደር ትራንስፖርትና መገናኛ ያላቸው ሚና እጅግ ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል። የዚህ ዘርፍ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ያለበትን ደረጃ ማወቅና ለአጠቃላይ ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በትክክል ሊገልጹ የሚችሉ የእስታቲስቲክ መረጃዎች መኖርና አስፈላጊነት ግልጽ የሆነ ዓላማ ያለው ነው።

በቅድመ አብዮትም ትራንስፖርትና መገናኛን የሚመለከት መረጃ በይዘቱና በስፋቱ ውሱን ቢሆንም በዓመታዊ የእስታቲስቲክስ መሽሔት እንደሚወጣ ይታወቃል። ይሁን እንጂ የአብዮታችን ሂደት ጥልቀት እያገኘ በመሄዱ የዚህን ዘርፍ ዝርዝር የሥራ እንቅስቃሴ የሚያመለክት መረጃ በይዘትና በስፋቱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ጽ/ቤቱ ስለመነበት ከ1969 ጀምሮ እራሱን የቻለ ተጠማሪ መጽሔት በየዓመቱ እየታተመ ይሰራጫል።

የትራንስፖርትና መገናኛ ዘርፍ የየብስ፣ የባሕርና የአየር ትራንስፖርትንና የቴሌኮሙኒኬሽንን፣ የፖስታ፣ የሬዲዮና ቴሌቪዥን፣ የመጽሔትና የጋዜጦች አገልግሎትን የሚያጠቃልል ሲሆን ስለእነዚህ የሥራ መስኮች የሚሰበሰቡት መረጃዎች የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

- ስለ ብዛታቸውና ዓይነታቸው
- ሠራተኞች ብዛትና ደሞዝ
- የትራንስፖርት ታሪፍ
- የመንገደኞች ብዛት
- የተራገፈና የተጫነ ዕቃ መጠን
- ስለ መቀዕለ ንቀይ
- ስለደረሱት አደጋዎች
- ... ወዘተ.

5.9.3 <u>የዋጋዎች ጥናት</u>

5.9.3.1 <u>የአዲስ አበበ የችርቻሮ ዋጋ ጥናት — 1957</u>

የችርቻሮ ዋጋ ጥናት የተጀመረው በአዲስ አበበ ከተማ በ1957 ሲሆን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በየወሩ መረጃው በመሰብሰብ ላይ ይገኛል፡፡ ጥናቱ ሲጀመር መሠረተ ዓላማው:—

- የችርቻሮ ዋጋ ከምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ፣
- ለቤተሰብ ፍጆታ የዋሉትን ዕቃዎችና አገልገሎቶች ጠቅላላ ዋጋ ለመተመን፣
- የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ ለማዘጋጀት ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት በአዲስ አበበ ከተማ የመገበያያ ስፍራዎች ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ዕቃዎችና አገልገሎቶች የሚመለከት መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን ከ1958 ጀምሮ የዋጋ ኢንዴክስ በመውጣት ላይ ይገኛል፡፡

5.9.3.2 <u>በአንዳንድ ከተሞች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት — 1967</u>

ከአበዋታችን ፍንዳታ ወዲህ የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ዓላማው የሰፋ በመሆኑ ከ1967 ጀምሮ በተመረጡ በ23 ከተሞች በየሦስት ወሩ በአዲስ አበበ ከተማ በየወሩ ጥናቱ ቀጥሏል፡፡

የጥናቱ ዓላማዎች ከላይ ከተገለጹት በተጨማሪ የሚከተሉትን የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

- በተለያዩ የስርጭት ደረጃዎች መካከል ያሉትን የዋጋ ልዩነቶች ለማጥናት፣
- የዋጋ ቁጥጥር ባለበት ቦታ የቁጥጥሩን ተግባራዊነት ለመገምገምና ለማሻሻል፣
- የዋጋ ቁጥጥር ባልሸፈናቸው ቦታዎችና ዕቃዎች ሳይ የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግበት ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ፣
- የዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ምርትና ስርጭት በሚመለከት ፖሊሲ አውጪዎች ለሚወስዱት ውሳኔ እንዲያገለግል፣
- የምርትን ጠቅላላ ዋጋና የሀገር ሀብት ውጤትን ለማስላት፣

በዚህ ጥናት አማካይነት የሚሰበሰቡት መረጃዎች በየከተሞቹ ስለሚገኙት ዋና ዋና ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋ የሚመለከት ነው።

## 5.9.3.3 <u>በገጠር የአምራቾችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት — 1973</u>

በከተሞች ብቻ ተወስኖ የነበረው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ይዘትና ስፋት አግኝቶ ብሔራዊ የተቀናጀ የገጠር ሰርቬይ ፕሮግራም አካል በመሆን ከ1973 ጀምሮ በገጠር የአምራቾችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት በመካሄድ ላይ ይገኛል።

በገጠር የአምራቾችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት በከተሞች ከሚካሄደው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ጋር የዓላማ ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆን የሚከተሉት ተጨማሪ ዓላማዎች ናቸው።

- ፖሊሲ አውጭዎች ስለእርሻ ውጤቶች ምርትና ሥርጭት ለሚወስዱት ውሳኔ የሚያገለግል መረጃ ለማስገኘት፣
- ገበሬዎች በአምራች ደረጃ ለእርሻ ውጤቶች የሚያስከፍሉትን የዋጋ መጠን ለማወቅ፣
- በተለያዩ የስርጭት ደረጃዎች መካከል ያሉትን የዋጋ ልዩነቶችና በኢኮኖሚ ላይ የሚታየውን ለውጥ ለማጥናት፣
- የእርሻ ውጤቶችን በሚመለከት የአምራች ዋጋና የምርት መጠን መመዘኛዎች /ኢንዴክሶች/ ለማዘጋጀት፣

... /24

በዚህ ጥናት የተሰበሰቡትና የሚሰበሰቡት መረጃዎች ገበሬው ለገበያ ያቀረባቸው የልዩ ልዩ ምርቶች ዋጋና በገጠር ገበያ ሊገኙ የሚችሉ የአርሸና የኢንዱስትሪ ውጤቶችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ናቸው፡፡

የጥናቶቹን ውጤት በሚመለከት በየጊዜው ሪፖርቶች እየተዘጋጁ ታትመው ተሰራጭተዋል፡፡

5.9.4 ዓመታዊ የአስታቲስቲክስ መጽሔት — 1955

"ዓመታዊ የአስታቲስቲክስ መጽሔት" በሚል ስም የሚታወቀው የጽ/ቤቱ ዋና መጽሔት ስለአገሪቷ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታ የሚገልጽ ልዩ ልዩ አስታቲስቲካዊ መረጃዎች ይዞ ስለሚገኝ ለብሔራዊ ዕቅድ ዝግጅት፣ ለፖሊሲ ቀየሳና ለልማት ፕሮግራሞች ብሎም ለምርምርና ለአስተዳደር ተግባሮች በመነሻነት ያገለግላል ተብሎ ስለታመነበት ከ1955 ጀምሮ እስከ 1976 እየታተመ ወጥቷል፤ ለወደፊትም በተሻለ ሁኔታ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

የዚህ መጽሔት ይዘት በየወቅቱ እየሰፋ የመጣ ቢሆንም ቀደም ሲል እንደተገለጸው ስለሕዝብ፣ ስለገብርና፣ ስለኢንዱስትሪዎች፣ ስለትራንስፖርትና መገናኛ ስለዋጋዎች ሁኔታ የሚገልጹ አስታቲስቲካዊ መረጃዎች ጠቅለል ባለ መልክ ተቀናብረው በመጽሔቱ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የመጽሔቱን ዝግጅት የተሟላ ለማድረግ ከተጠቀሱት ሌላ በተጨማሪ ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ከሚገኙ መዝገብት ላይ በየጊዜው ብዛት ያላቸው መረጃዎች ተሰብስበው በመቀናበር በመጽሔቱ ታትመዋል፡፡

እነዚህ ተጨማሪ መረጃዎች ቀጥሎ ስለተዘረዘሩት ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች የሚገልጹ ናቸው፡፡

1ኛ/ ስለ ማዕድን ኤሌክትሪክና ሕንጻዎች

2ኛ/ የውጭ ንግድ

3ኛ/ የመንግሥት ገንዘብና የቴክኒክ እርዳታ

4ኛ/ ዓመታዊ የሀገር ሀብት ውጤት

5ኛ/ የገንዘብ ድርጅቶች/ባንክና ኢንሹራንስ/

6ኛ/ ትምህርት፣ ጤና፣ ሕግና ፍትሕ

7ኛ/ ስለዕቃዎች ዋጋ

8ኛ/ የአየር ሁኔታ

.../25

## 6. የጽ/ቤቱ የኮምፒውተር፣ የማተሚያና የትራንስፖርት አገልግሎት እድገት፣

### 6.1 የመረጃ ማቀነባበሪያ /የኮምፒውተር/ አገልግሎት

የአስተዳደር፣ የጥናትና ምርምር፣ እንዲሁም ሌሎች ተግባራትን በዘመናዊ አሠራር ለማከናወን የኮምፒውተር መሣሪያዎች የሚሰጡት አገልግሎት ማስረጃ የሚያስፈልገው ባይሆንም እነዚህ መሣሪያዎች የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በማቀነባበር ረገድ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን መረዳት ያሻል፡፡

በመሆኑም በ1957 ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የተደረገው የኮምፒውተር መሣሪያ በዓይነቱ መካከል የሆነ፣ በፍጥነቱና በአፈጻጸም ቅልጥፍናው በወቅቱ ዘመናዊ ከተባሉት መሣሪያዎች በጣም ዝቅተኛ የነበረ፣ በየወሩ የአሜሪካን ብር 1,977 ኪራይ እየተከፈለ እስከ 1960 አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ ከ1961 ጀምሮ በጊዜው የተሻሉ ናቸው እየተባለ የመሣሪያዎችን ዓይነት በማስቀየር ብዙ ሺህ ብር በየወሩ ኪራይ እየተከፈለ እስከ 1973 ሲሠራበቸው ቆይቷል፡፡

ከ1973 ጀምሮ ጽ/ቤቱ ከመንግሥት ድጋፍ በማግኘቱና በአሠራር የተጠናከረ በመሆኑ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች ማለትም FAO, UNICEF እና UNDP ጋር ባደረገው ስምምነት ለሕዝብና ቤቶች ቆጠራ፣ ለተቀናጀ የገጠር ሰርቬይ ፕሮግራምና ለሌሎች ጥናቶች ውጤት ማቀነባበሪያ እንዲሆንና የመረጃ ማቀነባበሪያ አገልግሎት፣ በስፋት ለሚካሄዱ ጥናቶች ወሳኝ መሆኑን በማሰብ የተሻሉና ዘመናዊ የሆኑ የኮምፒውተር መሣሪያዎች በእርዳታ ተገኝተዋል፡፡ ስለሆነም በየወሩ ይወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሪ ከማዳንም በሸገር የጽ/ቤቱ የመረጃ ማቀነባበር አቅም ሊያድግ ችሏል፡፡

በዚሁ መሠረት ጽ/ቤቱ በ1976 የተካሄደውን ታሪካዊውን የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት ለማቀነባበር 113 የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠርና በዓታ ኢንኮደርስ አሠልጥኖ ሥራው እንዲከናወን አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ከጊዜ ወደ ጊዜ በአቅሙ እየተጠናከረ የመጣው የመረጃ ማቀነባበሪያ አገልግሎት ከጽ/ቤቱ ሥራ ውጪ ለሌሎች 18 ለሚሆኑ መንግሥታዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ፣ እርዳታና አገልግሎት ሰጥቷል፡፡

... /26

## 6.2 የማተሚያ አገልግሎት

ከእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት ተግባራት መካከል አንዱ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማቀነባበር በመጽሔት ልዩ ልዩ ሪፖርቶችን በማሳተም ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት ነው:: ለዚህ ተግባር አስተዋጽኦ የሚያደርግ የማተሚያ አገልግሎት በቅድመ አብዮት በጽ/ቤቱ የነበረ ቢሆንም አቋሙ ዝቅተኛ ስለነበር፣ በነበሩት ጥቂት መሣሪያዎች በመጠቀም አነስተኛ የሆኑትን የጽ/ቤቱን ሥራዎች በማከናወን ተወስና ነበር:: እንደ መጽሔቶችና መመሪያዎች የመሳሰሉትን ለማ ባተም፣ ለመስፋትና ለመጠረዝ ለተለያዩ ማተሚያ ቤቶች በጨረታ እየተሰጠ ይሠራ እንደ ነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው::

ከአብዮቱ ወዲህ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራንና ሌሎችንም ጥናቶች በተቀናጀና በተጠናከረ ሁኔታ በስፋት ለማካሄድ በተደረገው ጥረት፣ የሥራው እንቅስቃሴ የተ ሟላና የተሻከ እንዲሆን የሕትመት ክፍሉ መጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ማለትም UNICEF, UNFPA እና FAO ጋር የቅ ርብ ግንኙነት በመፍጠር በርካታና የተለያዩ የማተሚያ መሣሪያዎች በአርዓታ ተገ ኝቷል::

በመሆኑም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የነበረው የሕትመት አገልግሎት በአሁኑ ወቅት ለአንድ ማተሚያ ድርጅት የሚያስፈልጉትን መሣሪያዎች በዓይነትና ብዛት አሟልቶ በመጠናከሩ ብዛት ያለውን የጽ/ቤቱን አጠቃላይ የሕትመት ሥራዎች ከማከናወን አልፎ ከ14 ለሚበልጡ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች በአርዓታ ከፍተኛ አገልግሎት አበርክቷል::

## 6.3 የትራንስፖርት አገልግሎት

ለሀገር ልማትና እድገት በሚደረገው ሁለገብ እንቅስቃሴ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ በተለይም ለታዳጊ አገሮች ያለው የወሳኝነት ሚና ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል::

በዚህ የትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ የታየውን እድገት ለማመልከት እን ዲቻል በ1966 እና በ1979 የነበረውን ሁኔታ መግለጹ አስፈላጊ ይሆናል::

በ1966 የነበሩት ተሽከርካሪዎች ብዛት 49 ሲሆን በ1979 ያሉት ተሽከርካሪዎች ብዛት ወደ 142 ከፍ ብሏል:: ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በአብ

ዱቶ ዓመታት የተጨመሩት ተሽከርካሪዎች ብዛት 93 ናቸው። ይሕም የሚያመ
ለከተው እድገቱ ከፍተኛ መሆኑን ነው።

ምንም እንኳን በጽ/ቤቱ የተሽከርካሪዎች እድገት ከፍተኛ ቢሆንም፣
በሶሻሊስት መርህ በአሠራር የመ/ቤቶችን የጋራ ትብብር አስፈላጊነት በመገንዘብ
ጽ/ቤቱ ለልዩ ልዩ መንግሥታዊ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በተለያዩ ጊዜያት ከ38
የሚበልጡ ተሽከርካሪዎችን በእርዳታ ሰጥቷል። ስለዚህ በአሁኑ ወቀት አገልግሎት
በመስጠት ላይ የሚገኙት ተሽከርካሪዎች ብዛት 101 ብቻ ናቸው።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት የሦስቱ አገልግሎቶች ሁኔታ ሲገመገም በአ
ብዮታችን ዓመታት ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በተደረገው ስምምነትና
በተገኘው እርዳታ በጽ/ቤቱ በኮምፒውተርና በሕትመት መሣሪያዎች እንዲሁም በተሽ
ከርካሪዎች ዓይነትና በሌሎች ቁሳቁሶች የተደረገው ኢንቨስትመንት ከፍተኛ መሆኑና
በእነዚህ አገልግሎቶች የጽ/ቤቱ መጠናከር መጠቀስ ያለበት የአብዮቱ አመርቂ
ውጤት ሆኖ ይገኛል።

... /28

## 7. የበጀትና የሰው ኃይል አጠቃቀም ሁኔታ፣

### 7.1 የበጀት አጠቃቀም

ከ1964 ጀምሮ እስከ 1979 ድረስ በእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት አማካይነት ለተካሄዱ የእስታቲስቲክስ ሥራዎች ከመንግሥት የተፈቀደውና ከውጭ አገር በእርዳታ የተገኘው የመደበኛና የካፒታል በጀት መጠን በሠንጠረዥ ከዚህ በታች ቀርቧል።

| የበጀት ዓመት | መደበኛ በጀት /በብር/ | ካፒታል በጀት /በብር/ | | ጠቅላላ ድምር /በብር/ |
|---|---|---|---|---|
| | | ከአገር ውስጥ | ከውጭ አገር እርዳታ | |
| 1964 | 1,248,656 | — | — | 1,248,656 |
| 1965 | 1,348,376 | — | — | 1,348,376 |
| 1966 | 1,458,826 | — | — | 1,458,826 |
| 1967 | 1,585,322 | 797,500 | 3,824,381 | 6,207,203 |
| 1968 | 1,553,695 | — | — | 1,553,695 |
| 1969 | 1,556,875 | — | — | 1,556,875 |
| 1970 | 1,578,339 | — | — | 1,578,339 |
| 1971 | 1,652,365 | — | — | 1,652,365 |
| 1972 | 1,715,573 | — | — | 1,715,573 |
| 1973 | 1,948,313 | 5,296,900 | 6,106,700 | 13,351,913 |
| 1974 | 2,254,420 | 5,456,300 | 1,093,600 | 8,804,320 |
| 1975 | 2,432,878 | 3,711,900 | 2,910,500 | 9,055,278 |
| 1976 | 2,389,532 | 12,582,000 | 3,445,000 | 18,416,532 |
| 1977 | 2,565,870 | 3,430,200 | 1,417,500 | 7,413,570 |
| 1978 | 2,434,628 | 3,446,400 | 109,100 | 5,990,128 |
| 1979 | 2,487,412 | 4,766,800 | 300,000 | 7,554,212 |

... /29

ከዚህ በላይ እንደሚታየው የመደበኛ በጀት እንቅስቃሴ በአጠቃላይ መልኩ አድገት አያሳየ የመጣ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የ1979 መደበኛ በጀት ከ1964 መደበኛ በጀት ጋር ሲነጻጸር 99.2% አድገት አሳይቷል፡፡ የካፒታል በጀት ከ1973 ጀምሮ በየዓመቱ በመንግሥት ተፈቅዶ ሥራ ላይ መዋል የጀመረ ሲሆን ከውጭ አገርም በእርዳታ ተገኝቷል፡፡ ከ1973 ጀምሮ የካፒታል በጀት መፈቀድና መገኘት አብዮታዊ መንግሥት ለአስታቲስቲክስ ሥራ ከፍተኛ ግምት መስጠቱን የሚያመለክት ሲሆን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሥራውም በተጠናከረ ሁኔታ ስፋትና ጥልቀት እያገኘ በመካሄድ ላይ ነው፡፡

በተለይም የ1973 እና የ1976 የካፒታል በጀት ከሌሎች ዓመታት በጣም ጉልቶ ይታያል፡፡ የሁለቱ ዓመታት ካፒታል በጀት ከፍ ማለት በሚከተሉት ምክንያቶች ቀሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

1ኛ/ ብዙ ጥናቶችን ያቀፈ ብሔራዊ የተቀናጀ የገጠር ሰርቬይ ፕሮግራም የተጀመረው በ1973 በመሆኑ፣

2ኛ/ ለሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ቅድመ ዝግጅት የካርታ ሥራ በ1973 ተጀምሮ በ1976 የተጠናቀቀ ስለሆነ፣

3ኛ/ በአገሪቷ የመጀመሪያ የሆነውና ከፍተኛ የሆነ ገንዘብና የሰው ኃይል የጠየቀው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በ1976 የተካሄደ መሆኑ ሲጠቀሱ ከሚገባቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

7.2 <u>የሰው ኃይል አጠቃቀም</u>

ከአሥር በማይበልጡ ሠራተኞች የተጀመረው የጽ/ቤቱ ሥራ በየጊዜው በዓይነትም ሆነ በብዛት እየጨመረ በመምጣቱ በ1966 226 ቋሚ ሠራተኞች ነበሩ፡፡ በ1979 ደግሞ የጽ/ቤቱን ሥራ በማንቀሳቀስ ላይ ያሉት ሠራተኞች ጠቅላላ ብዛት 1,569 የደረሰ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 380 ቋሚ ሠራተኞች ሲሆኑ 1,189 የኮንትራት ሠራተኞች ናቸው፡፡

የ1979 ና የ1966 የቋሚ ሠራተኞች ሁኔታ ሲነጻጸር 68.1 በመቶ አድገት አሳይቷል፡፡ በቅድመ አብዮት የአስታቲስቲክስ ሥራ ውሱን ስለነበረ የኮን

ትራት ሠራተኞች አልነበሩም፡፡ ከአብዮቱ ወዲህ በተለይም ከ1973 ጀምሮ የአስታቲስቲክስ ጥናቶች በስፋትና በጥልቀት በመካሄድ ላይ ስለሚገኙ ይህን ተገበር በሚገባ ለማከናወን የኮንትራት ሠራተኞች ሚና ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ቁጥራቸው በየዓመቱ ከሥራው ስፋት ጋር እድገት በማሳየት ላይ ሲገኝ፣ በ1973 በጽ/ቤቱ የነበሩት የኮንትራት ሠራተኞች ቁጥር በ1979 ካሉት የኮንትራት ሠራተኞች ቁጥር ጋር ሲወዳደር 49.2 በመቶ አድጓል፡፡

በጽ/ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ የኮንትራት ሠራተኞች ተሳትፎ በአብዛኛው በመስክ ሥራ ማለትም በመረጃ ሰብሳቢነት ሲሆን አንዳንዶቹ ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተጠናቅረው በሪፖርት አስከ ወጡበት ጊዜ ድረስ ያሉትን ልዩ ልዩ ሥራዎች በማከናወን ይሳተፋሉ፡፡ ከዚሁ አንጻር የአስታቲስቲክስ ሥራ በስፋት መካሄድ የቁጥር ሁኔታ በኮንትራት ይሁን እንጂ የሥራ ዕድል በማስገኘት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

## 8. ያጋጠሙ አበይት ችግሮች፣

በአብዮቱ ዓመታት በጽ/ቤቱ የተከናወኑት ተገበራትና የተገኙት ውጤቶች የተገለጹ ቢሆንም እነዚህ ክንውኖችና ውጤቶች ያለምንም ችግር የተካሄዱና የተገኙ ስላልሆነ ማቅረቡ አስፈላጊ ነው፡፡

በጽ/ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ በማድረግና በተለይም ለዕቅድ አፈጻጸም አስቸጋሪ ከሆኑት ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1ኛ/ በየጊዜው በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ላይ ያለውን የጽ/ቤቱን ሥራና የሰው ኃይል ባለው ቢሮ ለማስተናገድ ባለመቻሉ የቢሮ ጥበት ሁኔታ ቋሚ የጽ/ቤቱ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡

2ኛ/ ከመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የሚፈለገውን መረጃ በወቅቱና በሚፈለገው ጥራት ለማግኘት፣ በየጊዜው በመመላለስ ገንዘብንና ጊዜን በማባከን ከመጠየቅ ሌላ ምንም ማስገደጃ ኃይል ጽ/ቤቱ የሌለው መሆኑን መረጃ ሰጪ አካላት ስለተረዱ ያለመተባበርና አምቢተኝነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዷል፡፡

3ኛ/ ለሀገሪቷ ስታቲስቲክስ አሠራር እድገት የባለሙያዎች አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ከዚሁ አንጻር የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ሌላው የጽ/ቤቱ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡

4ኛ/ በብዛቱና በዓይነቱ እየሰፋ የመጣውን የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም፣ እንዲሁም በማዕከላዊ ደረጃ በዘመናዊ አሠራር ለመምራትና ለመቆጣጠር እስከ ዛሬ ያለው የጽ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር አጥጋቢ ስላልሆነ በዕቅድ አፈጻጸም ረገድ የተለያዩ ችግሮች መከሰታቸው አልቀረም፡፡

እነዚህ ችግሮች እስከ ዛሬ የነበሩና አሁንም መፍትሔ የሚሹ ሲሆኑ፣ ለአንዳንዶቹ አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡

9. <u>በኢሕድሪ ምሥረታ ዋዜማ የስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሚገኝበት ሁኔታ፣</u>

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በአብዮቱ ዓመታት ባካሄዳቸው መራራ ትግሎች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ ዘርፎችና በባህል መስኮች የተወሰዱት እርምጃዎችና የተገኙት ውጤቶች ወደ ከፍተኛው የሶሻሊዝት እድገት ደረጃ ለመድረስ ጠንካራ መሠረት የጣሉ ሲሆን በዚህ ጠንካራ መሠረት ላይ በተስተካከለ አደረጃጀት ትክክለኛውን አመራር በመስጠት የግንባታው ሂደት ቀጥሏል፡፡ በዚህ የእድገት ጉዞ ሶሻሊስት ኅብረተሰብን በሙሉ ይዞቶ ለመገንባትና የሰፊውን ሕዝብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎት በማሳደግ የተሟላ ኑሮ ለማጎናጸፍ የሚደረግ ጥረት ለመሆኑ አብዮታዊ መንግሥትና ኢሠፓ የወቅቱን ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ያወጡት የአሥር ዓመት የልማት መሪ ዕቅድና ለኢሕድሪ ምሥረታ የዘገጁት ከንውን ለዚህ ጉልህ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

የስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤትም የአገሪቷን ተጨባጭ ሁኔታዎች በመገምገም፣ በወቅታዊ ሁኔታዎች ሳቢያ በየጊዜው ከአብዮታዊ መንግሥት የሚወጡትን መርሀ ግብር በመከተል አቅሙ የፈቀደለትን ያህል ልዩ ልዩ እስታቲስቲካዊ ተግባራት ሲያከናውን መቆየቱ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ በተለይም በኢሕድሪ ምሥረታ ዋዜማ ላይ በምንገኝበት በአሁኑ ወቅት ጽ/ቤቱ ያለበትን ትክክለኛ ሁኔታ መግለጹ አስፈላጊ በመሆኑ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

.../32

1ኛ/ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በአሥሩ ዓመት መሪ ዕቅድም ሆነ በጊዜው ተጨባጭ ሁኔታዎች አስጠጓጅነት በአሁኑ ወቅት መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት የሰጠው ስለሆነ የሦስተኛ ዓመት ዕቅድ አካል በሆነው በ1979 የእርሻ አስታቲስቲክስን መረጃ ለማስገኘት በተካሄደው ጥናት ላይ መጠነኛ የአሠራር ለውጥ ተደርጓል፡፡

የተደረገ ለውጥ፡—

- አዲስ ገበሬ ማኅበራት በሣይንሳዊ ዘዴ የተመረጡ ሲሆን ቁጥራቸውም ከ500 ወደ 750 ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

- ተጨማሪዎቹ 250 ገበሬ ማኅበራት የተመረጡት ትርፍ አምራች ከሆኑት ሦስት ክፍለ ሀገር ማለትም ከሸዋ፣ ከጐጃምና ከአርሲ ሲሆን ይኸም የተደረገበት ምክንያት ከጥናቶቹ የሚገኘው መረጃ ይቀርብ የነበረው በሀገር አቀፍና በክፍለ ሀገር ደረጃ ብቻ ስለሆነ፣ የግብርናውን ጥናት ደረጃ በደረጃ በማስፋት በእነዚህ ክፍለ ሀገር በአውራጃ ደረጃም አስተማማኝና በቂ የሆነ የእርሻ አስታቲስቲክስ መረጃ ለማስገኘት በመታቀዱ ነበር፣

- የአምራቾች የሕብረት ሥራ ማኅበራትን በተመለከተ የእርሻ አስታቲስቲክስ ጥናት ይሸፍን የነበረው በተመረጡት ገበሬ ማኅበራት ውስጥ የሚገኙትን ብቻ ስለነበር በዚህ ዓመት ግን ማኅበራቱ በሙሉ በጥናቱ እንዲሸፈኑ ጥረት ተደርጓል፡፡

2ኛ/ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ በአስተማማኝ ሁኔታ ለመገምገም የሚያስችል በቂ የእርሻ አስታቲስቲክስ መረጃን በስፋትና በጥልቀት በአውራጃ ደረጃ ለማስገኘት የተጀመረው እንቅስቃሴ የሚቀጥልና ሁሉንም ክፍለ ሀገር ደረጃ በደረጃ የሚሸፍን ቢሆንም በ1980 የዕቅድ ዓመት አራት ተጨማሪ ክፍለ ሀገር /ሲዳሞ፣ ባሌ፣ ወለጋና ጐንደር/ በስፋት፣ ለማጥናት ታቅዷል፡፡

3ኛ/ የወደፊቱን የእድገት አቅጣጫን በማገናዘብ በየጊዜው መሻሻልና መከናወን ያለባቸውን በማጤን፣ ለተሻለ ውጤት ከፍተኛ ጥረት እንደሚያሻ በውል በመረዳት እስከዛሬ ድረስ በገጠር ብቻ ሲካሄድ

... /33

የቆየውን ብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ስርቬይ ፕሮግራም
በተመሳሳይ ሁኔታ በከተሞችም በማቋቋም በ1980 የተለ
ያዩ ጥናቶች ለማካሄድ ታቅዷል፡፡ በዚህ ፕሮግራም
አማካይነት በተወሰኑ ከተሞች ሲካሄዱ የታቀዱት የጥናቶች
ዓይነት፡—

- የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት
- የሰው ኃይል ጥናት
- የጤና ጥናት
- የአመጋገብ ጥናት
- የቀጋዎች ጥናት

ሲሆኑ ሌሎች የቋሚነት ፀባይ ያላቸው እንደ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የውጭ ንግድ፣ የትራንስፖርትና መገናኛ የመሳሰሉት ጥናቶች የሚቀጥሉ ይሆናሉ፡፡

4ኛ/ የጽ/ቤቱ የ1979 በጀትና የሰው ኃይል አጠቃቀም ሁኔታ ሲገ
መገም፣ በአንዳንድ ወቅታዊ ሥራዎች ልዩ ከሚሆኑት ዓመታት
በስተቀር እስከ ዛሬ ከተፈቀደው በጀትና ከነበረው የሰው ኃይል
ከፍተኛውን ደረጃ ይዞ ይገኛል፡፡ ለመጥቀስ ያህልም በ1966
ብር 1,458,826 የነበረው በጀት በ1979 ብር 7,254,212
ደርሷል፡፡ እንዲሁም በ1966 226 የነበረው የቋሚ ሠራተኞች
ብዛት በ1979 ከፍተኛ እድገት በማሳየት ወደ 380 ቋሚና
1,189 የኮንትራት ሠራተኞች ከፍ ብሏል፡፡

ይህ ከፍተኛ የሆነ እድገት ሊገኝ የቻለው በፊት ትኩረት ያልነበረው የአኃዛታቲስቲክስ ሥራ በአብዮታዊ መንግሥት አስፈላጊነቱ ታምኖበት ከ1973 ጀምሮ በየዓመቱ የካፒታል በጀት በመፈቀዱ ነው፡፡ ሁኔታው ወደፊትም ይበልጥ በመጠናከር የሚቀጥል ሲሆን በሚቀጥሉት የዐቅድ ዓመታት አስተማማኝና በቂ የሆነ ብሔራዊ የአ ስታቲስቲክስ መረጃ የተሟላ እንዲሆን በሚደረገው ጥረት በበጀትና በሰው ኃይል ከፍተኛ እድገት እንደሚኖር ከወዲሁ መገመት አያስቸግርም፡፡

5ኛ/ መስተካከልና መዳበር ያለባቸው የአሠራር ሁኔታዎች፡—
ለማዕከላዊ ዕቅድ ዝግጅት፣ ለዕቅድ ክትትልና ቁጥጥር እንዲ
ሁም ለፖሊሲ ውሳኔ አሰጣጥ፣ ለምርምር፣ ለአስተዳደርና ለሌሎች መሰል
ተግባራት በመሠረታዊነት የሚያገለግሉ አስታቲስቲካዊ መረጃዎች በስ-

ፋትና በጥራት በብሔራዊ ደረጃ ተሟልቶ መገኘት አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡ ይህን ተግባር እውን ለማድረግና በየጊዜው በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ላይ ያለውን የመረጃ ፍላጎት በሚያረካ ሁኔታ ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኝ ገና መስተካከልና ማዳበር ያለባቸው የአሠራር ሁኔታዎች፣ እንዲሁም መወገድ ያለባቸው የአፈጻጸም ችግሮች ይገኛሉ፡፡

እነዚህም፡—

ሀ. ብሔራዊ አስታቲስቲክስ አንዲዓብር ማንኛውም አስታቲስቲካዊ አሠራር ማዕከላዊነትን የተከተለ እንዲሆን ማድረግ፣

ለ. የአሽታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት ተመስርቶ በሁሉም መ/ቤቶችና ድርጅቶች ተገባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣

ሐ. የጽ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር ተጠናክሮ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር ከፍል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲኖሩትና ደረጃ በደረጃ በሠለጠነ የሰው ኃይልና ማቴሪያል እንዲጠናከር ማድረግ፣

መ. በመረጃ አሰጣጥ፣ አስተሳሰፍና አዘጋጃጀት የመ/ቤቶችና ድርጅቶች እምቢተኝነትና አለመተባበር ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ስለሆነ ሁኔታው እንዲሻሻል አስፈላጊውን ማድረግ መጠቀስ ከሚገባቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

6ኛ/ በተለይም የ10ሩ ዓመት መሪ ዕቅድ አካል በሆነው በሦስቶ ዓመት የአስታቲስቲክስ ሥራ እቅድ አፈያ ከ1980 ጀምሮ ዓመት የአስታቲስቲክስ ሥራ አቅድ አቢያ ከ1980 ጀምር ዓመት የአስታቲስቲክስ ሥራ እቅድ ... ከፍተኛ ትኩረትና ዝግጅት የሚደረግበት አጠቃላይ የግብርና ቆጠራ ከፍተኛ ትኩረትና ዝግጅት የሚደረግበት አጠቃላይ የግብርና ቆጠራ ሲሆን የቆጠራው ግንባር ቀደም ዓላማ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ አስመልክቶ በአገሪቷ የታረሰውን የመሬት ስፋትና አጠቃቀም፣ ከታረሰው መሬት የተገኘውን የምርት መጠንና የአመራረት ዘዴን፣ እንደዚሁም አርሶ አደሩ ከእንሰሳዎችንና የእንሰሳት ሀብት ብዛትን በዓይነት በማወቅ የልማት ፕላን ለመንደፍ፣ ፓሊሲዎችን ለማውጣት፣ የገጠሩን ሕዝብ ኑሮ ለማሻሻል ለሚወሰደው መሠረታዊ እርምጃ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማስገኘት ነው ።